ትክክለኛ የእጅ አስተጣጠብ ቅደም ተከተል



የኮሮናቫይረስ በሽታ ምንድን ነው?

የኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) በሽታ የመተንፈሻ አካልን የሚያጠቃ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ እና ሊድን የሚችል በሽታ ነው። በሽታው በብዙ አገሮች እየተስፋፋ፤ በበርካታ ሰዎች ላይም ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ይገኛል። በሽታው የያዛቸው ሰዎች በሃገራችን መኖራቸውን ተከትሎ አሁን ሁላችንም ለዚህ በሽታ ተጋላጮች ነን።

ሆኖም ሁላችንም በምናደርገው ጠንካራ ተሳትፎ የበሽታውን ስርጭት እና ጉዳት መቀነስ ይቻላል። እርስዎም ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ እና የኮሮና ቫይረስ የመከላከያ መንገዶችን በመተግበር ራስዎን እና ቤተሰብዎን ከኮሮና ቫይረስ በሽታ ሊከላከሉ ይችላሉ።

ለበለጠ መረጃ
በነፃ የስልክ መስመሮች
8335 ወይም **952**
ላይ ይደውሉ

የጤና ሚኒስቴር፣ ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH, ETHIOPIA
Ethiopian Public Health Institute

የኮሮናቫይረስ በሽታ ምልክቶች

ትኩሳት

ሳል

ለመተንፈስ መቸገር

የኮሮና በሽታ ምልክቶችን ሲያዩ

ትኩሳት፤ ሳልና የመተንፈስ ችግር በራስዎም ሆነ በቤተሰብዎ ካስተዋሉ፤ በመጀመሪያ ምልክቶቹ የታየበት ሰው ተለይቶ እንዲቆይ ያድርጉ።

በመቀጠልም በነፃ የስልክ መስመር **8335** ወይም **952** ላይ በመደወል የባለሞያ ምክርና እገዛ ያግኙ። ይህን በማድረግ የራስዎን እና የቤተሰብዎን ጤና ይጠብቁ።

የኮሮናቫይረስ በሽታን ለመከላከል

- እጅዎን በሳሙናና በውሀ ቶሎ ቶሎ ይታጠቡ። አሊያም አልኮል ባለው የጀርም ማጽጃ በማሸት ያጽዱ

- አይንዎን፣ አፍንጫዎን እና አፍዎን በእጅዎ ከመንካት ይቆጠቡ

- ከሰው ጋር የሚደረግ ማንኛውንም ንኪኪ ያቁሙ። ለሰላምታም ቢሆን ከመጨባበጥ፣ ከመሳሳም፣ ከመተቃቀፍ ይቆጠቡ።

- ሰዎች በሚበዙባቸው ቦታዎች አይገኙ፣ የግድ ከሆነም የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ይጠቀሙ፣ በመካከላችሁ ቢያንስ 2 የአዋቂ እርምጃ ያህል ርቀት እንዲኖር ያድርጉ



- በሚያስሉ እና በሚያስነጥሱ ጊዜ አፍ እና አፍንጫዎን በሶፍት ወይም ክርንዎን በማጠፍ ይሸፍኑ፤ የተጠቀሙበትን ሶፍት ወይም ተመሳሳይ ነገር በአግባቡ ያስወግዱ